# ምዕራፍ አንድ ፡

## ሙከራ ጥያቄ አንድ

I. የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ

1. ኢትዮጵያ የባህር በር ካላቸው ሀገሮች ውስጥ የምትመደብ ሀገር ናት፡፡
2. የኢትዮጵያ ፍጹማዊ መገኛ 3 ዲግሪ እና 25 ዲግሪ ሰሜን እንዲሁም ከ 35 ዲግሪ እና

   48 ዲግሪ ምስራቅ ነው ፡፡
3. የኢትዮጵያ መገኛ 12 ዲግሪ ኬክሮስ እና 15 ዲግሪ ኬንትሮስ ነው፡፡
4. ኢትዮጵያን በሰሜን ደቡብ ያሚያዋስናት ሃገር ሱዳን ነው ፡፡
5. ኢትዮጵያ በስተ ደቡብ ምስራቅ የምትዋሰነው ከኬንያ ጋር ነው ፡፡
6. የኢትዮጵያ አዋሳኝ ሀገሮች ብዛት ሰባት ናቸው፡፡

LIVEWORKSHEETS

7. መገኛ ሳይንሳዊ በሆነ አግባብ አንድን ቦታ በካርታ ላይ የምናሳይበት መሳሪያ ነው ፡፡

8. በካርታ ላይ የአንድን ቦታ መገኛ በፍጹማዊ መገኛ ዓይነት ብቻ በመጠቀም ማሳየት ይቻላል፡፡

9. ኬክሮስን እና ኬንትሮስን በመጠቀም የአንድን ቦታ መገኛ የምናሳይበት መንገድ

   አንፃራዊ መገኛ ይባላል፡፡

10. በፍፁማዊ መገኛ የአንድን ቦታ መገኛ በአሃዝ ልኬት ለመግለጽ ይቻላል፡፡

11. የአንድን ሃገር መገኛ አዋሳኝ ሀገሮችን በመጠቀም  በፍፁማዊ መገኛ መግለጽ ይቻላል፡፡

12. ፍጹማዊ መገኛ አንድን ቦታ በየብስ ወይም በውሃ ክፍል የሚገለጫ ዘዴ ነው፡፡

II. በ "ሀ" ረድፍ የተቀመጡትን የኢትዮጵያ አዋሳኝ ሀገሮች በ "ለ" ረድፍ ከተቀመጡት ጋር በማዛመድ ትክክለኛውን ቁጥር በባዶ ቦታው ላይ ሙሉ

| ሀ | ለ |
| --- | --- |
| 1. ኬንያ | .............በስተ ደቡብ ምዕራብ |
| 2. ጂቡቲ | ...............በስተ ደቡብ |
| 3. ሱዳን | ................ በስተ ሰሜን |
| 4. ኤርትራ | ............... በስተ ሰሜን ምስራቅ |
| 5. ሶማሊያ | ............... በስተ ምዕራብ |
| 6. ደቡብ ሱዳን | ............... በስተ ደቡብ ምስራቅ |

LIVEWORKSHEETS

## III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ

1. ከሚከተሉት ውስጥ የኢትዮጵያ አዋሳኝ ሀገር ያልሆነው የትኛው ነው ?

ሀ) ኬን ያ　　ለ) ጂቡቲ　　ሐ) ግብጽ　　መ) ሱዳን

2. በሳተላይት አማካኝነት ዓለም አቀፋዊ በሆነ ሁኔታ ቦታዎችን የምናሳይበት ዘዴ የትኛው ነው ?

ሀ) ጂፒኤስ　　ለ) ጉግል ኧርዝ　　ሐ) ጎግል ካርታ　　መ) ካርታ

3. ከሚከተሉት ውስጥ የ ጂ.ፒ.ኤስ ጥቅም ያልሆነው የቱ ነው ?

ሀ) ተጓጉዦች በአየር፣ በባህር እና በመሬት ያሉበትን እና የሚሄዱበትን ቦታ ይለዩበታል።

ለ) አንድ ቦታ ከሌላ ቦታ የሚገኝበትን ርቀት ለማወቅ ያስችላል፡፡

ሐ) የሰዎችን እንቅስቃሴ ለማወቅ ይረዳል፡፡

መ) የአንድን ቦታ ፍፁማዊ መገኛ ለማወቅ ያስችላል

ሰ) የተለያዩ ካርታዎችን ለማዘጋጀት ይረዳል፡፡

4. የሳተላይት ምስሎችን፣ የአየር ላይ ፎቶግራፎችን፣ የጎዳና ካርታዎችን የሚያካትት መተግበሪያ ምን ይባላል?

ሀ) ጂፒኤስ　　ለ) ጉግል ኧርዝ　　ሐ) ጎግል ካርታ　　መ) ካርታ

5. ......................... እጅግ በጣም የታወቀ እና በስፋት ጥቅም ላይ የዋለ ጂኦግራፊያዊ የመረጃ ስርዓት መተግበርያ ነው፡፡

ሀ) ጂፒኤስ　　ለ) ጉግል ኧርዝ　　ሐ) ጎግል ካርታ　　መ) ካርታ

6. ከሚከተሉት ውስጥ ንድፍ ካርታ ለመስራት የሚያስችሉ መመሪያዎች ያልሆነው የትኛው ነው ?

ሀ) ካርታዎቻቸው የሚዘጋጁ ቦታዎችን መለየት

ለ) የቦታዎችን መነሻ እና መድረሻ ማስቀመጥ

ሐ) የቦታውን ንድፍ ካርታ በሀሳብ ማስቀመጥ

መ) የሚሳለውን ካርታ ድንበር መወሰን

ሰ) የድንበሩን መስመሮች በመክፈል በአራት ማዕዘን ቦታውን ማስቀመጥ

LIVEWORKSHEETS

7. ካርታ አዘጋጆችን መረጃን እንዲፈጥሩ፣ እንዲያከማቹ፣ እንዲመለከቱ እና መስተጋብር እንዲፈጥሩ የሚያስችለው መተግበሪያ የትኛው ነው ?

ሀ) ጉግል ኧርዝ ሐ) ጎግል ካርታ ሀ) ጂፒኤስ መ) ሀ እና ለ

8. የኢትዮጵያ ፍጹማዊ መገኛ ከሰሜን እስከ ደቡባዊ ጫፍ ድረስ ስንት ዲግሪ ነው ?

ሀ) 12 ዲግሪ የኬክሮስ (Latitudes) ለ) 15 ዲግሪ የኬንትሮስ (Longitudes)

ሐ) 12 ዲግሪ የኬንትሮስ (Longitudes) መ) 15 ዲግሪ የኬክሮስ (Latitudes)

9. የኢትዮጵያ ፍጹማዊ መገኛ ከምሥራቃዊ ጫፍ እስከ ምዕራባዊ ጫፍ ድረስ ስንት ዲግሪ ነው ?

ሀ) 12 ዲግሪ የኬክሮስ (Latitudes) ለ) 15 ዲግሪ የኬንትሮስ (Longitudes)

ሐ) 12 ዲግሪ የኬንትሮስ (Longitudes) መ) 15 ዲግሪ የኬክሮስ (Latitudes)

10. ኢትዮጵያን በስተ ሰሜን በኩል የሚያዋስናት ከሚከተሉት የትኛው ሀገር ነው?

ሀ) ሱዳን ለ) ቀይ ባህር ሐ) ጂቡቲ መ) ኤርትራ

LIVEWORKSHEETS